# አመራር

*የግል አስተያየት፡- ከአያል ሰው ደሴ (ኅዳር፤ ሁለት-ሽህ-አራት ዓ/ም)   - ክፍል አንድ*

## “ለፓርቲዬ (ለድርጅቴ) ያለኝ ታማኝነት የሚያበቃው (የሚያከትመው) ለአገሬ ያለኝ ታማኝነት ሲጀምር ነው”፡፡

“ለፓርቲዬ (ለድርጅቴ) ያለኝ ታማኝነት የሚያበቃው (የሚያከትመው) ለአገሬ ያለኝ ታማኝነት ሲጀምር ነው” ("My loyalty to my party ends where my loyalty to my country begins") ሲሉ የተናገሩት ማኑኤል ሉዊስ ኩዌዞን ሞሊና (1878 - 1944) የተባሉት ከ1935 - 1944 (እ.አ.አ) የፊሊፒንስ ፕሬዝደንት የነበሩት ሰው ናቸው፡፡ እኚኽ ታላቅ ሰው አገራቸውን ከአሜሪካ ነፃ ለማውጣት በተደረገው ትግል መሣሪያ አንግበው የታገሉና በኋላም በምርጫ ተወዳድረው በአብዛኛው ( 67% በላይ) ሕዝብ ድምፅ ተመርጠው በፕሬዝደንትነት ያገለገሉና በሥልጣን ዘመናቸው በአገራቸው የመሬት ይዞታ እንዲሻሻልና አርሶ-አደሮች ሥር-ከሰደደ ጭቆናና ብዝበዛ እንዲላቀቁ፣ በንግድም ይሁን በማንኛውም ረገድ በአገራቸው ላይ የውጭ ባዕዳን ቀጥተኛ ተፅዕኖ እንዳይኖር፣ ስብጥርጥሩ የበዛ የአገራቸው ሕዝብ የተሻለ መግባባትና ብሔራዊ ቁርኝት እንዲኖረው በጥናት ላይ በተመሠረተና በተመከረበት ሁኔታ የሚግባባበት ብሔራዊ ቋንቋ እንዲኖረው፣ በአጠቃላይ የአገራቸውን ነፃነት ለማስከበር፣ የሕዝባቸውን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥና ኑሮውን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ሰው ነበሩ፡፡

የድርጅትና የአገር ጥቅም ሁል-ጊዜ አብሮ ሊጓዝ የማይችልበትና አልፎ-አልፎም ተፃርረው የሚገኙበት ጊዜ እንደሚኖር ግልጥ ነው፡፡ እንደዚኽ ዓይነት ክስተቶች ሲያጋጥሙ በቅርቡ የድርጅት ጥቅምና በዘለቄታው የአገር ጥቅም መኻል አንዱን ማስቀደም የግድ በሚሆንበት ጊዜ በተለይ በአመራር ላይ ያሉ ሰዎች የሚወስዱት ምርጫና የሚይዙት መሥመር እንደማንኛውም ውሳኔ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ፕሬዝደንት ኩዌዞንን ያጋጠማቸው ሁኔታ ያ ነበር፡፡ ሕይዎታቸውን ሰጥተው ከታገሉለት ድርጅታቸው ጊዚያዊ ጥቅም ይበልጥ ምርጫቸው ያገራቸውን ዘለቄታዊ ጥቅም ማስቀደም መሆኑን ለድርጅታቸው አባላትም ሆነ ለሕዝባቸው በይፋ ባሣወቁበት ጊዜ ያንን አቋም እንዲወስዱ ያደረጋቸውን ምክንያት ሲገልጡ ነው ከዚኽ በላይ “ለአገሬ ያለኝ ታማኝነት የሚጀምረው ለፓርቲዬ (ለድርጅቴ) ያለኝ ታማኝነት ሲያከትም ነው” ሲሉ የተናገሩት፡፡

ብዙ አገሮች ከቀውጢ ጊዜና ከአጣብቂኝ ሁኔታ እንዲወጡ፣ አልቆላቸዋል ከተባሉበትና ከወደቁበት እንዲነሱ፣ ሕዝባቸውም ከትርምስ፣ ከርስ-በርስ እልቂትና ሰቆቃ ድኖ በአዲስ ተስፋ የተሻለ አዲስ ሕይዎት እንዲኖረው ያስቻሉ መሪዎች በየጊዜው መኖራቸው ይታወቃል፡፡ በዘመናችን እንደ ክቡር ኔልሰን ማንዴላ ዓይነቶች ማለት ነው፡፡

መቸም ቢሆን በተለይ ለሥርዓትና ለማኅበረሰባዊ ለውጥ የሚደረግ ትግል ያለ-ድርጅት እውን ሊሆን አይችልም፡፡ ድርጅት ደግሞ የጠራ መርኅ፣ ግልጥና የሚጨበጥ ዓላማ ሊኖረው ይገባል፡፡ በአንድ አገር ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ትግል ባለ-ሦስት እግር ወንበር ላይ የቆመ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እነሱም <u>የጠራ መርኅና የማያሻማ ግብ</u>፣ ያ መርኅ ላይ የተመሠረተ <u>ጠንካራ ድርጅት</u> እና ድርጅቱ የተመሠረተበትንና የቆመበትን መርኅ ሣይለቅ የተተለመለትን ግብ ለውጤት እንዲበቃ የሚያስችልና ኃላፊነት የሚሰጠው (የሚወስድ) <u>ታማኛና ብቁ አመራር</u> ናቸው፡፡

በዚኽ አጭር ሃተታ በአጠቃላይ “አመራር” በሚለው በተለይም በሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ ሥር ለለውጥ የሚደረግ ትግልን ለግብ ለማብቃት በሚጠይቀው ይኽ ቁልፍ ክፍል ላይ ያሉኝን አንዳንድ የግል አሳቦች ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

እንደማንኛውም በዓላማ ዙሪያ የተደራጀ ክፍል የፖለቲካ ድርጅትም ለፖለቲካ መሥመሩ (መርኁ) ግብ መምታትና ለቆመበት ትግል መሣካት የተያዘው የትግል መሥመር ግልጥነትና ጥራት፣ ለግቡ ተግባራዊነት ተገቢና መጣኝ የሆነ አደረጃጀትና አወቃቀር መያዝ አስፈላጊ የመሆኑን ያኽል፣ መርኁን ጠብቆና የወጣውን የፍልሚያ ትልም በአግባቡ ተከትሎ አዳዲስና ወቅታዊ ስልቶችን እየነደፈ፣ ትግሉ የሚጠይቀውን ሁሉ እያሟላ ድርጅቱ ሕይዎት እንዲኖረውና የታለመውን ውጤት ለማስመዝገብ ይችል ዘንድ ለድርጅቱ ውድቀትም ሆነ ስኬት ተጠያቂና ኃላፊ የሚሆን፣ <u>ተኣማኒነት፣</u>

ወሳኝነትና ብቃት ያለው አመራር መኖሩ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የትግል ድርጅትን መምራት ደግሞ ሹመት ሣይሆን ኃላፊነት ነው፤ ከኃላፊነትም እጅጉን የከበደ ኃላፊነት፡፡ ማንኛውም ሰው ጠንካራም ግብዝም ተፈጥሮን አቀላልቅሎ የያዘ በመሆኑ፣ ማንኛውንም ቡድን ይሁን ድርጅት፣ በተለይም የትግል ድርጅትን የመምራት ኃላፊነት ከተጠያቂነትና አገልግሎት ከመስጠት መንፈስ ጋር ካልተዛመደና የድርጅቱ ፍልሥፍናና አወቃቀር የሰውን በጎ ጎን የማኮሰስና ደካማ ጎኑን አይሎ እንዲወጣ የማድረግ ሁኔታን የሚያመቻች ከሆነ፣ ድርጅቱ መሥመሩን የመሳት ዕድሉ ሠፊ ይሆናል፡፡

የአመራር ኃላፊነት በተሰጣቸው ግለሰቦች ላይ በወል እና በተለይም መሪ እንዲሆን/እንድትሆን አደራውና እምነቱ በተጣለበት/ባት ግለሰብ ትከሻ ላይ የወደቀ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም ይኽ ከባድ ኃላፊነት እንዲሁ በዘፈቀደ እና ባወጣ-ያውጣው ተብሎ የሚተው ወይም የሚጫን ሣይሆን በተገቢ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም ድርጅቱ የቆመው የሕዝብ ትግልን ለመምራት እስከ-ሆነ ድረስ የሰውን ደኅንነትና አልፎም ምትክ የሌለውን የሰው ሕይዎት የሚመለከት በመሆኑ ኃላፊነቱ በእጅጉ የከበደ ይሆናል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ታጋይ ድርጅት የፈለገውን ጥራት ያለው የፖለቲካ መሥመር ወይም ሕዝቡ አመኔታዊና ተስፋውን የጣለበት አቋም ቢኖረው፣ ድርጅቱን እንዲመሩ አደራው በተሰጣቸው መሪዎች ዘንድ ትግሉ ግቡን እንዲመታ የሚጠይቀውን መንፈሰ-ጠንካራነትና ለመርኅ ተገዥ መሆንን፣ ኃላፊነት ለግል ሣይሆን ለጠቅላላው መሆኑን ከልብ ማመንና መረዳትን፣ ሙሉ-በሙሉ ተጠያቂነቱና ታማኝነቱ ለሕዝብና ለአገር መሆንን  እንዲሁም ችሎታን፣ ቀናነትና ቆራጥነትን መጠየቁ የግድ ይሆናል፡፡ ማንኛውንም ድርጅት እንዲመራ/እንድትመራ ኃላፊነት የሚጣልበ/ባት ሰው ትግሉ እንዲሣካ በማድረግ አዎንታዊ ገጹም ሆነ የተጠበቀው ውጤት እንዳይገኝና ትግሉ እንዲልከሰከስ፣ የተከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ እንዲቀርና አልፎም በአንፃር የቆመውን ክፍል (መንግሥትም ሆነ ድርጅት) የሚያግዝና ለሕዝቡ ሰቆቃ መቀጠል አስተዋፅዖ አድራጊ የመሆንን ያኽል ታላቅ አሉታዊ ሚና እንደሚኖረው የታወቀ ነው፡፡

ብዙ ድርጅቶች ከያዙትና ከቆሙበት የትግል መሥመርና ከተከተሉት አደረጃጀት፣ ወዘተ.. ይበልጥ በአመራር እጦት ምክንያት ለውድቀት እንደተዳረጉ በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው፡፡ መጣኝና አስፈላጊ የትግል ትልም ባለመከተልም ይሁን ወቅታዊ የስልት ማስተካከል ባለማድረግ፣ መስዋዕትነት በመፍራትና ኃላፊነት ለመውሰድ ባለመድፈር ምክንያት ቆራጥና ወሳኝ እርምጃ ባለመውሰድም ይሁን ያላስፈላጊ መስዋዕትነት በማስከፈል፣ ወዘተ.. አንድን ድርጅት ለአዎንታዊ ውጤት እንዳይበቃ፣ አልፎም ለውድቀትና ለጥፋት ሊዳርግ መቻሉ አጠያያቂ አይመስለኝም፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች በቆራጥነታቸውና የተጠየቁትን መስዋዕትነት ለመክፈልና በአጠቃላይ ለሕዝብ ትግል ሕይዎታቸውን ለመስጠት መሰል የማይገኝላቸው አባላት ሳይገዷቸው፣ ሌሎች አሉታዊ ሁኔታዎች ቢጨመሩም በዋናነት ግን ተገቢና ብቁ አመራር ባለማግኘት ምክንያት ለውጤት አለመብቃት፣ አልፎም ያላስፈላጊ መስዋዕትነት ማስከፈልም ሆነ መልሶ ማገገም አዳጋች ወደ-ሆነ አቅጣጫና ለውድቀት ጭምር እንደሚዳረጉ በራሣችን የትግል ታሪክ የታየ ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያችን ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ክብርና ኩራት የሚንገበገቡና እራሣቸውንም አሣልፈው የሰጡ መሪዎች ነበሯት፡፡ ለአገርና ለሕዝብ ክብር የቆሙና መስዋዕትነት የከፈሉት ደግሞ አገር የመምራት ኃላፊነት የተጣለባቸው ወገኖች ብቻ አልነበሩም፡፡ ለአገር ክብርና ለኢትዮጵያዊ ማንነት የቆሙ፣ የተፋለሙ፣ መስዋዕትነት የከፈሉና ተከብረው ያስከበሩን ቆራጥ ዜጎች በየደረጃውና በየአካባቢው ነበሩ፡፡ አገራቸውና ሕዝባቸው ነፃነታቸውን ተገፍፈው በጣልያን ባዕዳን ወራሪዎች ሥር በወደቁበት ፈታኝ ወቅት ብዙዎች ለነዚኽ ባዕዳን ገንዘብ፣ ከንቱ ሹመትና ሽልማት ሸብረክ ብለው ኅሊናቸውን በመሸጥ በራሣቸው አገር የሁለተኛ-ደረጃ-ዜጋ መሆንን መርጠው ጌታ-አደር ሲሆኑ፤ በጣልያን የቀረበን ማንኛውም የሹመት፣ የሽልማትና የሃብት መደለያወች ሁሉ አሻፈረን በማለትና ጌጣቸውም፣ ክብራቸውም፣ ማዕረጋቸውና ሃብታቸው በምንም ዋጋ የማይተኩ ነፃነታቸው፣ አገራቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ማንነታቸው ብቻ እንደሆኑ ያስመሰከሩ ጀግኖች በመስዋዕትነታቸው አስከብረውናል፣ አንገታችንን ቀና አድርገን እንዲሄድ አስችለውናል፡፡ እንደነ ራስ አበበ አረጋይ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ራስ እምሩ ኃይለ-ሥላሴ፣ ራስ ውብነህ ተሰማ፣ ቢትወደድ አዳነ መኮንን፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ደጃዝማች ሣኅሌ፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ወዘተ.. የመሰሉ መሰል-የሌላቸው ጠንካራ የኢትዮጵያ ልጆች በቁጥራቸው ማነስ ተስፋ ሣይቆርጡና መጠን በሌለው የጠላት ዘመናዊ መሣሪያ ሣይረበሹ፣ አገሬ-ክብሬ ብለው መከራና ስቃዩን ሁሉ ተቀብለው በዱር-በገደል እየወጡ-

እየወረዱ፣ በተቻላቸው መጠን ወገኖቻቸውን እያደራጁ፣ ተስፋ በጨለመበት ሰዓት ተስፋ እየሰጡና አይዟችሁ እያሉ፣ ከፋሽስትና ከባንዳ ጥርቅም ጋር እየተዋደቁና መስዋዕትነት እየከፈሉ ታግለው በማታገል፣ ወቅቱ ለጠየቀው የአርበኝነት እንቅስቃሴ ቁርጠኛ አመራር በመስጠት ኢትዮጵያ በባዕዳን ወራሪ ጠላት ላይ ድል እንድትቀዳጅና ነፃነታችንን አስከብረን ከትውልድ-ትውልድ እንድንኮራና አንድነታችንን ጠብቀን እንድንዘልቅ አስችለውናል፡፡

እነኝኽ ጀግኖቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት የአገራችን ነፃነት ሲረጋገጥ በተጠየቁት መስክ አገራቸውን በቅንነት ለማገልገል ከመሠለፍ ውጭ ተከታዮቻቸውን ይዘው "ይኼ ካልተደረገልኝ" የሚል ጥያቄ አላቀረቡም፡፡ ያንን ያደረጉት ደግሞ መጀመሪያውኑ የታገሉት ለውለታና ለራሣቸው የግል ጥቅም ሣይሆን ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ስለነበር ነው፡፡

በዘመናችን ግን ያ እየተረሣ ይመስላል፡፡ በእርግጥ በተደራጀ መልክ ትግል ከተጀመረ አንስቶ ለራሣቸው ጥቅምና ዝና ሣይሆን ውድ ሕይዎታቸውን ለአገርና ለሕዝብ ዓላማዎች መስዋዕት ያደረጉ ዜጎች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ የዚያኑ ያኽል ግን አገርንና ሕዝብን ለመታደግ ወይም ወደ-ተሻለ ደረጃ ለመውሰድ የሚመሠረት ድርጅት ከመሥራቾቹ፣ ከአመራሩና ከጠቅላላ አባላቱ በላይ ለሆነ አገራዊና ሕዝባዊ ዓላማ መሆኑ እየታወቀ ብዙን ጊዜ ለድርጅት መመሥረት ቀዳሚ ሚና ያላቸው ግለሰቦች ድርጅቱን እንደ-ግል ኩባንያ (የንግድ ተቋም) የራሣቸው ብቻ ንብረት አድርገው በመቁጠር ጎልውናው ጭምር ከእነሱ የማይጠየቅ የበላይነትና የማይገሰስ ሥልጣን ጋር ሲያቆራኙት፣ እነሱ ካልመሩት የድርጅቱን አለመኖር እንደሚመርጡ በተግባር ታይቷል፡፡ ለዚኽ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የታጠቀ አመፅ (ትግል) የሚያደርጉ ድርጅቶችን የሚመሩ ግለሰቦች አብዛኛውን የትግሉ ባኅሪ የግድ ስለሚል ከድርጅታቸው ውጭ ባሉ ዜጎች ላይ ብቻ ሣይሆን በድርጅታቸውም ውስጥ ባሉ ታጋይ አባሎቻቸው ላይ ግድያን የጨመሩ ልዩ-ልዩ በኃላፊነት የሚያስጠይቁ እርምጃዎችን ስለሚወስዱ በድርጅት አመራር ላይ ያላቸውን መሪነትና ሙሉ ቁጥጥር ማጣትን የሚያዩት ለነዚያ አድራጎቶች ተጠያቂነትን ከመፍራት አኳያ ነው፡፡

ስለሆነም በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ እስከ-ዕለተ-ሞታቸው ድረስ ለጎልውናቸው ብቸኛ ዋስትና አድርገው ስለሚቆጥሩት የድርጅታቸውን የመሪነት ቦታ አይለቁም፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ድርጅታቸው የተፈጠረውና ያነገበው ዓላማ ለአገርና ለሕዝብ መሆኑ ቢታወቅም ለእነሱ ያ ድርጅት የእነሱን የግል ዓላማና የሥልጣን ፍላጎት ማስፈጸሚያ አድርገው ነው የሚቆጥሩት፡፡ የነ-አቶ መለስ፣ የአቶ ኢሣኢያስ የመሣሰሉትን እንተውና በተቃዋሚው ጎራ ከተሰለፉት ድርጅቶች መኻል ስንቶቹ ድርጅቶች ናቸው ከተመሠረቱ ጀምረው "ሊቀ-መንበር" ከተባሉ ግለሰቦች ሌላ ሰው መርቷቸው የማያውቅ? በእውነት ድርጅቶቻቸው ከእነኝኽ "ሊቀ-መንበሮች" ውጭ ኃላፊነቱን መሸከም የሚችል አባላት የሏቸውም ማለት ነው? ያ ከሆነስ ድርጅቱ "ሊቀ-መንበር" ከተባለው ግለሰብ የግል ሃብትነት በምን ይለያል? ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሊባልስ ይችላል ወይ? በድርጅት መሪነት ረገድ እነኝኽ "ሊቀ-መንበሮች" አገራዊ ሥልጣን አለመያዛቸው ካልሆነ ከእነ-አቶ መለስ በምን ይለያሉ? ድርጅታቸው ሥልጣን የመያዝ ዕድል ቢገጥመው እንደነ-አቶ መለስ/ኢሣኢያስ በድርጅታቸው አናት ላይ ቁጢጥ ብለው ፈላጭ-ቆራጭ የማይሆኑበት ዋስትና ምንድነው? "እናቴ በእንቁላሌ በቀጣሽኝ" እንዲሉ በተለይ ስለ-ዴሞክራሲ የምናነበንብ ክፍሎች ከወዲኹ የድርጅት መሪነት ጊዜያዊ ኃላፊነት እንጂ ድርጅትን በግል እርስትነት ሙጥኝ የሚባልበት አለመሆኑን፣ መምራት እንደምንፈልግ መመራትንም ማወቅ እንዳለብንና እንደምንችልም በተግባር ማሣየቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

አንዳንድ ድርጅቶች የቆሙትና አባሎቻቸውም የተጠየቁትን መስዋዕትነት ሁሉ የከፈሉትና የሚከፍሉት ለአገርና ለሕዝብ ዓላማዎች መሆኑ ቀስ-በቀስ እየተረሣ እራሣቸው ድርጅቶቹ፣ አንዳንዴም "መሪዎች" የተባሉት ዓላማ ሆነው ቁጭ ይሉና እነሱን መንካትና መንቀፍ ከመንገድ በወጣ መልኩ አገርና ሕዝብን መንካት ተደርጎ ሲቀርብም ተስተውሏል፡፡

***ይቀጥላል....***